# እንባ ውስጥ ሲቀመጥ

ከንጋቱ ያየህ ይራድ

ከፖለቲካው ስንክሳር፦ ከማደራጀት ከሰበካው፣
ከመታኮስ፦ ከመዋጋት፦ ከመማሩ፦ ከማስተማሩ---- ከቅስቀሳው፣
ከማያልቀው የግር መንገድ፦ ከረሃቡ ከጥማቱ----ከስብሰባው ከቱማታው።
ትግሉ ሁሉን በሸፈነበት፣
ትምሕርት----- የራስ ሕይወት------ የዘመድ የጓደኛ በተረሳበት፣
አካኪዘራፍ እንጂ ወደድኩሽ ወደድኩህ በተገዘተበት-----፤
ድንገት የገነፈለ ስሜት የፈነዳ የልብ ሲቃ፣
በትግል ጋቢ ያሸለበ እውነተኛ ፍቅር ሲነቃ።
ከጥይት ተኩሱ የበለጠ፣
መዝሙሩን ሁሉ የዋጠ፤
ከሁሉም በላይ የገነነ የሁሉን እንባ የቸረ፣
በትግል ለወደቀ ጓደኛ የተጻፈ ግጠም ነበረ።
«ዛሬም አልተለያየንም ቃል ኪዳናችን አልተጣሰ፣
ዛሬም አልተነጣጠልን ትዳራችንም አልፈረሰ------
የእንግዳ ቤት ነው እንደድሮው ጎጆአችን አልቀዘቀዘ፣
ጣራውም አላፈሰሰ ቀለሙም አልደበዘዘ-------
ውድ ጓድ አልደብቅህም ብቸኝነት ግን ይሰማኛል----
መልክህን ማየት እጓጓለሁ ስምህን መጥራት ያምረኛል---»
መታገሉን እየታገለች፤ በቆራጥነቱ ኮርታበት፣
መዝሙሩን እየዘመረች መልኩን እያየችበት፣
ማስተማሩን እያስተማረች እሱን ምሳሌ አድርጋበት፣
ለመሰዋት ተነስታ ሞትን ከባሏ አይታበት፣
ብስጭት ስትል ብቸኝነት ሲሰማት፣
እሱን ማጣቱ ሲያሳዝናት፣
ሞቱን መቀበል ሲከብዳት፣
ታወራው የነበረ ፍቅረኛዋ ሳቅፈገግታው ሲታወሳት፣
መዝገብነሽ ብእሯን አነሳች ሰቆቃዋ እንዲቀጣላት።
አልሞትክም አለችው ፍቅረኛዋን፣
አልረሳሁህም አለችው ፍቅረኛዋን።
ፍቅር ከትግል በኋላ ተብሎ በተሰበከበት፣
መዋደድ ወንጀል በሆነበት፣
ዘመድ መናፈቅ በተኮነነበት፣
የሂሩት የፈቅር ትዝታ ግጥም የተዳፈነውን አጋየበት።
ግማሹ አንገቱን ሠብሮ እንባውን አነባበት፣
ያገለደመውን ኩሹክ {ቁራጭ አንሶላ} አፍንጫውን አበሰበት።
ታዲያ የት አለች  መዝብነሽ ብል  በቅደምለት
ሞተች አሉኝ ባሜሪካ፣
ባልታወቀ ሰው በካራ{በጩቤ} ተወግታ
እንዳለችው እንደ ሕልሟ፤ ባሏን እንባውስጥ አስቀምጣ፣
ደስባሏትም ሳትደሰት የራባትን ያክል ሳትበላ ጥሟን ለማርካት ሳትጠጣ---
ሞተች አሉኝ ከባሏ ጋር ተቀላቀለች፣

በትግሉም በስደቱም እንባዩ ውስጥ ተቀመጥ እንዳለች።